# አውደ ኢትዮጵያ

ሚያዚያ 15 2008 የኢትዮጵያ ሕዝብ ዲሞክራሲን ህጋዊ መንግሥትንና ፍትሃዊ ስርዓትን የመጠየቅ መብት አለው! እትም 27

## ሞት አይቀሬ ሆነና፤የማይሞት ሰው ሞተ

### የሃዘን መግለጫ መልእክት ከኢንጂነር ግዛቸዉ የአንድነት ም/ሊቀመንብር

ሚያዚያ 12 ቀን 2001 ዓ.ም

ጥላሁን ገሰሰ ስንል ሙዚቃ፤ ሙዚቃ ስንል ደሞ ጥላሁን ነው። ሙያና ሙያተኛ ተጋብተው ለዘመናት አላንጳች መቃቃር መኖር መቻላቸዉ እንዲህ በዋዛ የሚገኝ ጉዳይ አይደለም።መግባባትን፤መከባበርን ይጠይቃል።

ጥላሁንና ሙዚቃ ደግሞ እንዲህ ናቸው። መግባባት ብቻ ሳይሆን ተዋደው ነው የዘለቁት። ዛሬ ጥላሁን ቢለየንም ዜማዎቹ ዘላለማዊ ሆነው የሚኖሩ፤ ዘመን የማይሽራቸው፤ትውልድ የማይረሳቸው ጥንዶች ናቸው።

አሁንም ጥላሁን ቢለየንም ሙዚቃው ከኛው ጋር አብሮን ነዋሪ በመሆኑ ጥላሁንና ሙዚቃ እንዳይለያዩ ያደረጋቸዋል። በመሆኑም ጥላሁን በዜማዎቹ ውስጥ ህያውነቱ ዘላለማዊ ሆኖ ይኖራል።

ጥላሁን ስለምን አዚምዋል ብለው የሚጠይቁም አሉ። የሚቀለው ግን ስለምን አላዜመም የሚለዉን ጥያቄ መጠየቅ ነዉ። ለዚህ ጥያቄ መልሱም ቀላል



ነዉ። «ምንም» ስለሚሆን።

ጥላሁን የሃገር ጉዳይና፣ የህዝብ ጉዳይን በተመለከተ ማንም አይቀድመው።አለሁ ብሎ ፊት ለፊት ነው ተስልፎ የሚገኘው።

በሺ ዘጠኝ መቶ ሰባ ስባት ምርጫ ወቅት፣ ለምርጫ ቅስቀሳ በሚያደርግበት ወቅት፣ ቅንጅት ይጠቀምበት የነበረው አንድ ዜማ ነበር። እርሱም «ኢትዮጵያ» የተሰኘውን የጥላሁን ገሰሰ ዜማ ነበር። ጥላሁን በደስታ እንድንጠቀምበት ፈቅዶልን በዚያ ዜማ መልአክታችንን ሕብረተሰቡ አጣጥሞ እንዲያዳምጠን ለማድረግ ተችሏል።

ለጥላሁን የምንቸረው ከበሬታ ድንበር የለሽ ነው።ሕዝብ ያከብረዋል፤ሀገር ያከብርዋል፤ይህም ከበሬታ ከትውልድ ትውልድ ይተላለፋል።

በፓርቲያችን አንድነት ለፍትሕና ለዴሞክራሲ፤ባመራሩና በመላው አባላት ስም መሪር ሀዘናችንን አየገለጽን፤ ፈጣሪም ነፍሱን በጻድቃን ማረፊያ እንዲያሳረፋት አንለምነዋለን።

ለቤተስቡም መጽናናትን አየተመኘን፤የሙያው አፈቃሪዎችም ጥናቱን እንዲሰጣችውና በዜማው ዘልአለማዊነት ሞቱን እንዲያሸነፉት አናሳስባለን።

ከፍ ካል አክብሮት ጋር

ግዛቸው ሽፈራው

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓረቲ ም/ሊቀ መንበር

የድርጅት ጉዳይ ሃላፊ

## የመሪዎች እዉቀት !

ከ ማሕደር ሰላማዊ

በአገራችን በመሪነት ደረጃ ብቅ ያሉት ሁሉ፣ ሙሉ ለሙሉ አንድ አይነት ናቸዉ ባይባልም አብዛኛዉን ጊዜ የሚያመሳስላቸዉ የ«እናወቃለን» ቅዠት አለባቸዉ። ቅዠታቸዉ ደግሞ እዉን ወደ መሆን የሚሸጋገረዉ በእርግጥ እዉቀትና ብቃት ኖሯቸዉ ሳይሆን በዙሪያቸዉ የሚኮለኮሉ፣ እዉቀት ያላቸዉ ግን እዉነትን ለመናገር የማያደፍሩ ሰዉ-ተብዬ ግኡዛኖች ጎሽ ጎሽ ስለሚሏቸዉን ፣ ምስክር ስለሚሆኑላቸዉ ነዉ።

በቀዳሚነት ቀድሞ አገራችን ኢትዮጵያን ለ17 አመታት ሲያምሳትና ሲያተራምሳት የነበረዉን የደርግን ዘምን እንመልከት።

ኮሎኔል መንግስቱ ኃያለማሪያም በአካባቢያቸዉ ካሉት ከአብዛኞቹ ባለሥልጣናት በትምህርት አነስ ያሉ ነበሩ። በዙሪያቸዉ ደግሞ በሙያቸዉ አንቱ የተባሉ ምሁራን ነበሩ። በየሰለጠኑበት ሞያ የሚሰጡት አስተያየት በአገር ብቻ ሳይሆን በሰለጠነዉ ዓለምም ቢሆን ተቀባይነት ያለዉ እንደነብረና የተከበሩ እንደነበሩ የሚነገርላቸዉ በርካታዎች ነበሩ።

እየቆየ ወደኋላ ገደማ ግን ዉሎ ሲያድር ምሁራኑ እያወቁ ስህተትነቱን ከመናገር ይልቅ ለተቀመጡበት ወንበርና ለሚቦጨቅላቸው ጥቅማ ጥቅም በማደር፣ በዝምታ ማላፋቸዉ ሊቀመንበሩን ያወቁ አስመሰላቸዉ።

ይህ ሁኔታ ዉሎ እያደረ ነገሮችን እያከረረ መጣ። አንድ ያኔ ሲወራ የነበረ አንድ ታሪክ ነበር። አንድ ቀን ኮሎኔል መንግስቱ ኃያለማሪያም በአይሮፕላን ሲያልፉ፣ አርንጓዴ የለበሰ የተንጣለለ መሬት ያዩና በአይሮፕላኑ ዉስጥ ለነበሩ የእርሻ ባለሞያና ባለሥልጣን «ይህ ቦታ ከፍተኛ የእርሻ መንደር ሊሆን ስለሚችልና የሩዝ ምርት ደግሞ ለሕዝባችን ተለዋጭ ምግብ ሊሆን ስለሚችል፣ ሩዝ ይዘራበት» ይላሉ። እኚህ የ'እርሻ ባለሞያና አብረዋቸዉ የነበሩ ሌሎች ባለሥልጣናት መሬቱ ለሩዝ እርሻ እንደማይሆን ለመናገር የደፈረ አልተገኘም። ሌላዉ ቢቀር ለሩዝ እርሻ መሟላት ያላባቸዉ ሊሟሉ እንደማይችሉ የሚናገር በመጥፋቱ ሩዝ እንዲዘራ መመሪያ መመሪያ ተሰጠ።

ትእዛዙን የተቀበሉት የእርሻ ባለሞያ በእዉቀታቸዉና በችሎታቸዉ በሰለጠኑበት ከመሄድ ይልቅ በጊዚያዊ የስልጣን ፍቅር በመታወር ምሁርነታቸዉን ሁሉ በመሃይምነት ለዉጠዉ፣ እንደማይሆን እያወቁ፣ ሰራተኞ አስምጥተዉ፣ ዉሃ አስቆፍርዉ፣ ኩሬ ፈጥረዉ ሩዝ እንዲዘራ አደረጉ። ላይለማ ላያፈራ፣ ፈሪዉ ራስ ወዳድ ባለሞያ ሹመኛም ዉጤቱን ቀድመዉ እያወቁት።

ይህን ትእዛዝ የሰጡት ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማሪያም፣ የትእዛዛቸዉን ዉጤት ለመስማት ወይም ለማየት አስበዉ ሳይሆን፣ በአጋጣሚ ደግመዉ ወደዚያ አካባቢ በአይሮፕላን ይበራሉ። ሰፈሩ አካባቢ ደርሰዉ ወደ ታች ሲመለከቱ ምርት ቀርቶ ምንም የለም። እኛም በሆዳቸዉ ዕውቀታቸውን የካዱ ባለስልጣን፤ሃሳብ የገባቸዉ የእርሻ ባለሞያ ይህን ጊዜም ከኮሎኔል መንግስቱ ጋር ነበሩ።

ኮሎኖኔል መንግስቱ ድንገት «የታለ ሩዙ ?

ወደ ገጽ 3 ዞሯል

## አንብበው ለወገን ያሰተላልፉ

# ለሶስት አመት የተዘጋ በር ተከፈተ - በአዲስ አበባ የተደረገዉ ሰልፍ

ኢትዮጵያ ታልቅ ሰዉ በዚህ ሳምንት አጥታለች። የተሰማንን ትልቅ ሐዘን እየገለጽን እግዚአብሄር የጥላሁንን ነፍስ በጻድቃንና በሰማዕታት ጋር እንዲያኖር ለቤተሰቦቹና ለወዳጆቹ ሁሉ መጽናናት ይሰጥ ዘንድ ጸሎታችን ነዉ።

በዚሁ ሰሞንም ከምርጫ 97 በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ በአኢትዮጵያ ዉስጥ በተቃዋሚ ፓርቲ የተጠራ ሰላማዊ ስለፍ ተደርጉዋል።

ሚያዚያ 30 ቀን 1997 ዓ.ም ነበር ታላቁ ሕዝባዊ ትሱናሚ ተብሎ የሚታወቀዉ ሰላማዊ ሰልፍ የተደረገዉ። ፍጹም ኢትዮጵያዊ ጨዋነት በተሞላበት፣ የኢትዮጵያ አረንጉዋዴ፣ ቢጫ ቀይ ባንዲራ በሰፊዉ እያዉለበለቡ ፣ ከሶስት እስከ አራት ሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዉያን፣ ከግንቦት 1991 ዓ.ም ጀምሮ በኢትዮጵያ የተዘረጋዉና በጎሳና በዘር ላይ የተመሰረተዉን ፖለቲካ በቁርጠኝነት «እምቢ» በማለት፣ «ኢትዮጵያዊነትን› እና አንድነትን አንግበዉ ድምጻቸዉን ለማሰማት ወጡ።

ብዙም አልቆየም በምርጫ መሸነፉንና ለአመታት ሲያራምደዉ የነበረዉን የኋላ ቀር ፖለቲካ በሕዝብ መተፋቱን የተረዳዉ ገዥዉ ፓርቲ፣ ጸረ-ዲሞክራሲያዊ ተግባራትን በመፈጸም የጉልበትና የጡንቻ እርምጃዎች መወሰድ ጀመረ። እራሱ ያጸደቀዉንና እመራበታለሁ የሚለዉን ሕገ መንግስት በይፋ መርገጡን ተያያዘዉ።

በአንቀጽ 9 ንኡስ አንቀጽ 1 «ሕገ መንግስቱ የሀገሪቱ የበላይ ሕግ ነዉ። ማንኛዉም ሕግ፣ ልማዳዊ አሰራር፣ እንዲሁም የመንግስት አካል ወይም ባለሥልጣን ዉሳኔ፣ ከዚህ ሕገ መንግስት ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈጻሚነት አይኖረዉም» ሲል ከሕገ መንግስቱ በላይ ምንም ነገር እንደሌለ በግልጽ ያስቀምጣል።

ይህ የአገሪቱዋ የበላይ የሆነዉ ሕግ፣ ስለ ዜጎች የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግና ሃሳባቸዉን በግልጽ የመናገር መብት ምን እንደሚል በአጭሩ ለማየት እንሞክራለን።

ሕገ መንግስቱ በአንቀጽ 30 ንኡስ አንቀጽ 1 ላይ ሲዘረዝር «ማንኛዉም ሰዉ ከሌሎች ጋር በመሆን መሳሪያ ሳይዝ በሰላም የመሰብሰብ፣ ሰላምዊ ሰልፍ የማድረግ ነጻነትና፣ አቤቱት የማቅረብ መብት አለዉ። » ይላል። ሰላማዊ ሰልፎች በሚንቀሳቀሱባቸዉ ቦታዎችና በሕዝብ እንቅስቃሴ ላይ ችግር እንዳይፈጠር ለማድረግ ሕገ መንግስቱ አግባብ ያላቸዉ ስርዓቶች ሊደነገጉ እንደሚችል በንኡስ አንቀጽ 2 በመግለጽ፣ ሰልፈኞች በየትኛዉም አገር እንደሚደረገዉ ሰልፍ ከመዉጣታቸዉ በፊት ለሚመለከታቸዉ አካላት ያሳዉቃሉ።

## ርዕሰ አንቀጽ

በዚህ መሰረት ነበር እንግዲህ፣ በሚያዚያ 30፣ የቅንጅት አመራር አባላት በመስቀል አደባባይ ሰልፍ እንደሚያደርጉ አሳዉቀዉ፣ በዚያ ሰልፍም መንግስት ፖሊሶችን መድቦ፣ በአንድ ሰዉ ላይ ጉዳት ሳይደርስ በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ በሰልፉ ተገኝቶ፣ በሰላም ወደ ቤቱ የተመለሰዉ።

ይህ ሕዝብ በሚያዚያ 30 ጨዋነቱን፣ ሕግ አክባሪነቱን በግልጽ አሳይቷል። እንደዚያም ሆኖ ግን ከምርጫ 97 በኋላ እንደገና ሰልፍ እንዳይወጣ ሕዝቡ ታግደ።

የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9 ንኡስ አንቀጽ 2 «ማንኛዉም ዜጋ፣ የመንግስት አካላት፣




የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ሌሎች ማህበራት እንዲሁም ባለሥልጣኖቻቸው፣ ሕገ መንግስቱን የማስከበርና ለሕግ መንግስቱ ተገገር የመሆን ሃላፊነት አለባቸዉ።» ይላል።

አንቀጽ 74 የጠቅላይ ሚኒስትሩ የሥራ ሃላፊነትና ግዴታን ይዘረዝራል። ንዉስ አንቀጽ 12 እና 13 ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሕገ መንግስቱና በሌሎች ሕጎች የተሰጡትን ሌሎች ተግባራት የማከናወን፣ ሕገ መንግስቱንም ማክበርና ማስከበር እንዳለበት በግልጽ ይደነግጋል።

እንግዲህ ሕገ መንግስቱ የሚለዉ እንዲህ ሆኖ እያለ፣ አቶ መለስ ዜናዊ ሕገ መንግስታዊ ሃላፊነታቸዉን ወደ ጎን በማድረግና እራሳቸዉን ከሕግ መንግስቱ በላይ በማድረግ፣ በሕገ መንግስቱ የተደነገገዉን መብት ሲረግጡ ነዉ ያየነዉ። ሕገ መንግስቱ የዜጎች ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ መብትን ቢደነግግም፣ አቶ መለስ ዜናዊ ሰላማዊ ሰልፍ እንዳይደረግና ዜጎች እንዳይሰባሰቡ የማድረግ ሕገ መንግስታዊ መብቶችን በአዋጅ ከለከሉ።

አቶ መለስ ዜናዊ ይሄንን ሕገ ወጥ ተግብራቸዉን ሲወስዱ ለአገር ደህንነት በማሰብ እንደሆነና ሕገ መንግስቱም በአንቀጽ 93 ልዩ ድንጋጌውችና አስቸኳይ አዋጆች ማወጣት እንደሚቻል በመፍቀዱ ነዉ የሚሉ ክርክር የሚያነሱ አንዳንድ የገገርው ፓርቲ ካድሬዎች ይኖራሉ።

አንቀጽ 93 ንኡስ አንቀጽ አንድ ግን፣ መቼ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መዉጣት እንዳለበት በማያከራክርና በማያወላዳ መልኩ ሲያስቀምጥ «የዉጭ ወረራ ሲያጋጥም ወይም ሕገ መንግስታዊ ስርአቱን አደጋ ላይ የሚጥል ሁኔታ ሲከሰትና በተለመደዉ የሕግ ማስከበር ስርዓት ለመቋቋም የማይቻል ሲሆን፣ ማናቸዉም የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የሕዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት፣ የፌደራል መንግስት የሚኒስትሮች ምክር ቤት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የመደንገግ ስልጣን አለዉ። የተፈጥሮ አደጋ ሲያገጥም ወይም የሕዝብን ደህንነት አደግ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት የክልል መስተዳድሮች በክልላቸዉ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሊያዉጁ ይችላሉ።» ይላል።

የአስቸኳይ ጊዘ አዋጅ ሊታወጅ የሚችለዉ ሶስት ቅድመ ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ እንደሆነ እናያለን። እነርሱም የዉጭ ወራሪ ሲያጋጥም፣ ሕገ መንግስትዊ ስርዓቱን አደጋ ላይ የሚጥል አደጋ ሲፈጠርና የሕዝብን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል እንደ በሽታና የተፈጥሮ አደጋ አይነት ሲከሰት ብቻ ናቸዉ።

በምርጫ ዘጠና ዘባት ኢትዮጵያን የወረረ አንዳችም ወራሪ ጠላት አልነበረም። ሕገ መንግስታዊ ስርዓቱንም ለመናድ አዲስ አበባን እየዞረ ያለ የታጠቀ ኃያል አልታየም። እንደዉም ሰላማዊና ፍጹም ጨዋነት በሞላበት ሁኔታ፣ ሕገ መንግስቱ በሚፈቅደዉ መሰረት የአመራር ለዉጥ እንዲመጣ የድምጽ ካርዱን ይዞ ሲንቀሳቀስ ነዉ የታየዉ። የተፍጥሮ አደጋ በተመለከተ በዚያን ወቅት ጎልቶ የወጣ ትልቅ አደጋ አልሰማንም።

ስለዚህ አቶ መለስ ዜናዊ የወሰዱት እርምጃ በምንም መልክ ሆነ ሚዛን አንቀጽ 93 ያስቀመጣቸዉን ቅድመ ሁኔታዎች የሚያሟላ አልነበረም። ማንም ማንበብ የሚችል፣ ፊደል የቆጠረ ኢትዮጵያዊ የተወሰደዉ እርምጃ ፍጹም ሕገ ወጣ እንደሆነ መደምደማቸዉ አይቀሬ ነዉ።

አቶ መለስ ዜናዊና ድርጅታቸዉ በራሳቸዉ ያለመተማመን ትልቅ ችግር ስላለባቸዉ፣ ከምርጫ ዘጠና ሰባት በኋላ ማናቸዉንም አይነት ሰላምዊ ሰልፎችን ሳይፈቅዱ ቆይተዋል። ባለመፍቀዳቸዉና የሕዝቡን ሕገ መንጋትዊ መብት በመርገጣቸዉም ከምርጫ ዘጠና ሰባት በኋላ አንዳችም ሰላምዊ ስለፍ በኢትዮጵያ ዉስጥ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ሊደረግ አልቻለም።

ገገርዉ ፓርቲ በተለይም በአንድነት ፓርቲ

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የመሪዎች እዉቀት ...

ከገጽ 1 የዞረ

» ብለዉ ይጠይቃሉ። ባለሥልጣኑም «ወቅቱ ስላልሆነ አልያዘም፣ ወቅቱ ሲደርስ እንደገና ልንዘራዉ እየተዘጋጀን ነዉ» ሲሉ አሁንም እንደማይበቅል እያወቁ ሞያቸዉን ያዋርዳሉ። ኮሎኔል መንግስቱ ምንም ሳይሉ ጉዞዉ ቀጠለ።

ከጥቂት ቀናት በኋላ እኝህ ባለስልጣን ወደ ሊቀመንበር መንግስቱ ቢሮ ተጠርተዉ « የሩዙ ጊዜ ገና ቢሆንም ያንተ ጊዜ ደርሷልና በእጅህ ያለዉን ንብረት አስረክበህ ቦታህን ልቀቅ» ተብለዉ በቃል ተሰናበቱ።

የዚህ በወርደት የተባረረ የእርሻ ባለሞያ አይነት ተግባር የፈጸሙና አሁንም ባለዉ መንግስት ስር እየፈጸሙ ያሉ፣ በራስ መተማመን ብሎ ነገር የሌላቸዉ፣ ለጥቅም የተገዙ፣ አወቀዉ የማያወቁ፣ ተምረዉ እንዳልተማሩ የሆኑ፣ አይነ እያላቸዉ የታወሩ፣ ጆሮ እያላቸዉ የማይሰሙ ደናቁርት በርካታ ናቸዉ።

የበላይ አካልን « አይሆንም፣ ይሄ እንደታሰበዉ ቢፈጸም ይሄን፣ ያንን፣ ጉዳት ያስከትላል» ብለዉ በሙያቸዉ ብቃት ተማምነዉ፣ የተማሩበትንና የሰለጠኑበትን የማይጥሉ፣መሪዎችም ሲሳሳቱ የሚወቅሱና የሚገስጹ በአሁኑ ዘመን በወያኔ አምባ መኖራቸዉን እጠራጠራለሁ።

አሁን በስልጣን ላይ ባለዉ መንግስት የተፈጸመ፣ በደርግ ዘመን የምናወቀዉ “የመዉረስ» ፖለቲካ አይነት አሳዛኝ ክስተት ይችን ሰሞን ተፈጽሟል።

ቀድም ብሎ፤ከኢትዮጵያ ቡና ላይ ቶክሲክ አለ በሚል ባለፈዉ አመት ጃፓን የኢትዮጵያ ቡና ወደ አገሯ እንዳይገባ እግዳ እድርጋ እንደነበረ የሚታወስ ነዉ። በቀናት፣ ጃፓን እገዳዉን ከማድረጓ በፊት ግን የቡናዉ ግኝኙነት እንዲቀጥል በማሰብ፣ በወቅቱ ችግር ሆኖ የነበረዉ ቶክሲክ በቡናዉ ላይ መኖር አለመኖሩን በተመለከተ ምርመራ ለማድረግ አንድ የባለሞያ ቡድን ወደ አዲስ አበባ ትልካለች።

ቡድኑ አዲስ አበባ እንደገባ በቡና ባለሥልጣናት ገንቢ ያልሆነ ዘገባ ሕወሃት በሚቆጣጠራቸዉ መገናኛ ብዙሃን ይሰነዘራሉ። የተሰነዘሩትን አስተያየቶች በመገናኛ ብዙሃን ሲዘገብ ጃፓኖቹ ሲያዩ ይገረማሉ። መግለጫዉ ‹‹ስም ለማጥፋት ለተንኮል ተብሎ የተነዛ ወሬ እንጂ አንዳችም ቶክሲክ በቡናዉ ላይ እንደሌለ›› የሚገልጽ ነበር።

መግለጫዉንም የሰጡት የቡና ባለሥልጣናት ጃንን ባለሙያዎች «ቶክሲክ ስለሌለ» በሚል ምርምራቸዉን እንዲያቆሙ ስላልጠየቁዋቸዉ የጃፓን ባላሞያዎች፣ መግለጫዉን አይተዉ ለጊዜዉ ግራ ቢጋቡም ስራቸዉን ቀጠሉ።

ጃፖኖች ምርመራቸዉን አጠናቀዉ ወደ አንድ ድምዳሜ ደረሱ። ቶክሲክ መኖሩ ተረጋገጠ። ነገር ግን ቶክሲኩ ቡናዉ ላይ ሳይሆን ጆንያዉ ላይ ሆኖ ተገኘ። «ይህንን ጆንያ በሞላ ጣሉትና እኛ ንጹህ በሆነ ጆንያ በነጻ እንተካላችሁ። አሉ» ጃፖኖቹ።

የመንግስት ባለስልጣናት ግን ከግትርነታቸዉ የተነሳ እያወቁ የፈጸሙት ደባ ሃገርን እንደሚጎዳ ቢያዉቁም ለሃገር ባላቸዉ ደንታ ቢስነት ይህን ለመቀበል ፈቃደኛ ሊሆኑ አልቻሉም። ከጃፓን ጋር የነበረዉ የቡና ገበያም ቆመ። አገራችን የዉጭ ምንዛሪ አጣች። ጃፓን ግን ቡናዋን አላጣችም። ከሌላ ቦታ አገኘች።

ይህ ሁሉ ስህተት ሲፈጸም የቡና ባለስልጣናት የጃፓንን ችሮታ ቢቀበሉ፣ » በሚል ስጋትና ለአገር በማሰብ ሳይሆን ለግል ጥቅም በማሰብ ኢትዮጵያ የዉጭ ምንዛሪ እንድታጣ ያደረጉ ባለሥልጣኑ እንዲህ አይነት ትልቅ ስህተት ሲሰሩ በዙሪያቸዉ ያሉ ሌሎች ባለሞያዎችና የንግድ ኤክስፐርቶች «ይሄ ነገር እኮ አገር ይጎዳል። ዉሳኔዉ ትክክል ስላልሆነ ይታሰብበት» አላሉም ነበር። ለምን ? እነርሱም «ጌቶቻቸዉን ከማበሳጨትና ጥቅማቸው ከሚጎዳ አገር የራሷ ጉዳይ » ያሉ ደካማ እኩዮች ስለነበሩ ነዉ።

በአሁኑ ወቅት በዉጭ አገር ያለዉ የቡና ዋጋ አዘቅዝቋል። በአገር ቤት ያሉ የቡና ሻጮች የዉጪዎቹን ገዢዎች ጠባይ ስለሚያወቁ፣ ቡናዉን ከመሸጥ ለጊዜዉ በመጋዘን አስቀመጡ። መንግስት ደግሞ የዉጭ ምንዛሪ፣ በጋ እንዳባረረዉ ጎርፍ ደርቆበት፣ «ግቢ ነፍስ ዉጪ ነፍስ» እያለ ነዉ። አንዱ ሚኒስትር ተነስቶ «ቡናዉን ሽጡ» የሚል መልእክት አስተላለፈ። ነጋዴዉ ደግሞ የነጻ ገበያ በመሆኑ፣ የዉጭ ገዢዎች ዋጋዉን አወቀዉ እያጣጣሉ ስለሆነ፣ ትንሽ ብንቆይ የተሻለ ዋጋ እናገኛለን በሚል ሊሸጡ ፈቃደኛ አልሆኑም። የዉጭ ምንዛሪ ችግር ያለበት፣ ሕግ የማይገዛዉ መንግስት በአዲስ አበባ እንዳለ የሚያወቁት የዉጭ ቡና ገዢዎች፣ ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ በኢትዮጵያ ያለዉ ቡና እንደሚሸጥ ስለገመቱ ዋጋዉን የበለጠ አወረዱት።

ዉሎ ሲያደር የመንግስት ችግር ከመጠን በላይ በመሆኑ የሚመለከታቸዉ ሚኒስቴር ቡና ላኪዎችን ሰብስብ ይጠሩና በአዳራሽ ተገኙተዉ አጭርና ጥያቄና መልስ የሌለበት መመሪያ በሁለት መስመር በ 3 ደቂቃ ሰጥተዉ ዉልቅ ይላሉ። መመሪያዉ «ያከማቻችሁትን ቡና በአስቸኳይ ሽጡ። በቃ ሌላ የምለዉ የለም» ብለዉ በገቡበት በር ወጡ። ነጋዴዉም ተበተነ። ግን ቡናዉ አሁንም አልተሸጠም።

የዉጭዉ ገዢ ደግሞ ይሄንን ሲሰማ የቡናዉን ዋጋ እንደገና አወረደዉ። «ግዴታ ስለተጣለባቸው ሳይወዱ ይሸጣሉ። ያዉም በኛ ፍቃድና በምተምንላቸዉ ዋጋ» እያለ ፎከሩ።

ነጋዴዉ ደግሞ «እስቲ እንተያያለን። ቡናዉ ያለዉ በመጋዘናችን፤ የመጋዘናችንን ቁልፍ በእጃችን እንተያያለን» ብሎ ወሰነ። ቡና አልተሸጠም። መንግስት ያለዉ አንዱ የዉጭ ምንዛሪ ማግኛ መንገድ ይሄዉ በመሆኑ ጣልቃ መግባት አለብኝ ብሎ ወሰነ። የቡና ላኪዎችን እንደገና ማነጋገር ተፈለገ። ማን ቢያናግር ነጋዴው ይፈራል ተባለና ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዲያነጋግሩ ተደረገ። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን አንድም በጠቅላይ ሚኒስትሩ ዙሪያ የቡናም ሆነ የንግድ ባለሞያዎች አሊያም ኢኮኖሚስቶች፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሊወስዱ የሚገባቸዉ እርምጃ በአገር ቤት ያሉ ኢንቨስተሮችና ነጋዴዎች ላይ ሳይሆን እንደ ስታራ ባክስ ባሉ የዉጭ ቡና ገዢዎቻችንን የሚያንበረክክ መሆን እንዳለበት የነገራቸዉ ደፋር አልነበረም። በዚህ ላይ ደሞ እነ ስታር ባክስ ከላይ እስከታች ያሉትን የቡና ሰዎች በጥቅማ ጥቅም ጠፍንገው ይዘዋቸዋል፡፡ ለምን ቢባል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሰማይ በታች የማያወቁት ነገር የለም ብለዉ እራሳቸዉን አሳምነዉ የተቀመጡ በመሆናቸዉ ነዉ።

የጠቅላይ ሚኒስትሩና ቡና ላኪዎች ስብሰባ ደረሰ። በሰብሰበዉ «ሲነገራቹህ ለመስማት ፈቃደኞች አልሆናችሁም። ቡናዉን በመጋዘናቹህ ቆልፋችህ ላለመሸጥና በአጭር ጊዜ የቡናዉን ዋጋ ከፍ አድርጋቹህ ለመክበር በማሰብ የአገሪቱን የዉጭ ምንዛሪ ጎድታቹኋል። ስለዚህ በዚህ ሂደት ላይ በማን አለብኝነት መጋዘን የቆለፋችሁትን ነጋዴዎች እገሌ እገሌ እገሌ የተባሉት ድርጅቶች ከዛሬ ጀምሮ የቡና መላክ ፈቃዳቸዉ ተሰርዟል ። በመጋዘን ያለዉንም ቡና እኛ እንሸጠዋለን» በማለት 17 000 ቶን ቡና ወረሱ።

ይሄ ሁሉ ሲሆን «ይህ አካሄድ አደጋ አለዉ። የዉጭ ገበያዉን የልብ ልብ ይሰጣል» ብሎ አንድም ባለሞያ አፋን ለመክፈት አልደፈረም። ይህ በደርግ ዘመን የነበረዉን የመዉረስ ፖለቲካ ያስታወሰን የአቶ መለስ ሕገ ወጥ ማን አለብኝ ድርጊት ፣ ወሬዉ ለዉጭዉ ገበያ ደረሰ። የቡና ዋጋ በተለይም ጫናዉና ጣጣዉ የበዛበት ሙያተኛዉ ዲዳ የሆነበት የኢትዮጵያ ቡና ዋጋ ዝቅዝቅ ሄደ። «መንግስት ቀምቶ ሊሸጥ ስለሆነ መንግስት የዉጭ ምንዛሪ ዉጥረት ስላለበት በሰጠነዉ ዋጋ ይሸጣል» በሚል የነስታር ባክስ ትእቢትና የነ ጠቅላይ ሚኒስትር የእውቀት ማነስ የባለሙያዎች ለሆድ ማደር ቡናችን ተዋረደ። መንግስትም ቋምጦ ቀረ። መካሪ ያጣ ንጉስ ያለአንድ አመት አይነግስ ማለት ይህች ናት።

ቡናዉ ከባለቤቶቹ እጅ ወጥቶ በጉልበተኛ መንግስት ቢወሰድም፣ የዉጪዎቹ ገዢዎች የመግዛት ፍላጎት ግን በአቶ መለስ ፍጥጫና ግልምጫ፣ ማስፈራሪያትና ቡራ ከረዮ፣ ፋከራና ማን አለብኝነት የሚታዘዝ ወይም ለፍርሃት የሚዳረግ ባለመሆኑ የአቶ መለስ ቀራርቶ ሰሚ አላገኘም።

«ሕግን» እንደበትር መጠቀም ልማዳቸዉ የሆኑት አቶ መለስ ዜናዊም ይባስ ብሎ ሕጋዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ ይነግዱ የነበሩ ዜጎች ሊከሰሱ እንደሚችሉም በመግለጽ ዛቻና ማስፈራራት ጀምረዋል።

ይህ ሁሉ ስህተት ያመጣዉና ለዚሁ ከንቱ ዉጤት ጠቅላይ ሚኒስትሩን የዳረገዉ በዙሪያቸዉ ያሉ ባለሥልጣናት ናቸዉ። ገና አቶ መለስ ዜናዊ ለመናገር ሲያስቡ፣ እነዚህ ባለስልጣናት የደም ምታቸዉ እየጨመረ የአስቀድሞ ማስጠንቀቂያ ስለሚደርሳቸዉ በፍርሃት ምጣድ እየታመሱ እዉነቱን ለመናገር አልቻሉም። አቶ መለስ ዜናዊ ሲሳሳቱ፣ አሊያም በማያወቁት ሙያ ገብተዉ አለሥራቸዉ ሲፈተፍቱ እነዚህ በዚሪያቸዉ ያሉ ባለሥልጣናትና አማካሪዎች ዝምታን መረጡ። ይህ ደግሞ ለማንም አልበጀም። የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ አላሳደገም። የሲዉስ ባንኩንም የሂሳብ ሳጥን መጠን ከፍ አላደረገም።

# ብርቱካን ትፈታ

## ለሶስት አመት የተዘጋ...

ከገጽ 1 የዞረ

ሊቀመነበር ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ላይ የወሰደውን እርምጃ በመቃወም ፣ በነጻነት ሃሳባቸዉን መግለጽ የሚችሉት በባእድ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዉያን፣ ባለፉት ሶስት ወራት ብቻ ሶስት ታላላቅ ሰላምዊ ሰልፎችን በተለያዩ የአለማችን ግዛቶች ማድረጋቸዉ ይታወሳል። (የአለም አቀፍ ሰላምዊ ሰልፍ አስተባብሪዎች እንደደገለጹልን ይህ በኢትዮጵያዉያን የሚደረገዉ የተቃዉሞ ሰልፍ በተጠናከረና ተከታታይነት ባለዉ መልኩ እንደሚቀጥል ተረድተናል።)

በዚህ ሳምንት ግን ካልታሰበና ካልተጠበቀ ቦታ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ እንዲፈቱ የሚጠይቁ ድምጾችን ለመስማት ችለናል። በአዲስ አበባ ከ250 በላይ የሚሆኑ የአንድነት አመራር አባላትና ደጋፊዎች በአዲስ አበባ ከተማ የኢትዮጵያን አርንጉዋዴ ቢጫ ቀይ ባንዲራ እያዉለበለቡ፣ የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን ትልቅ ፎቶን አግንበዉ፣ ድምጻቸዉን ከፍ አድርገዉ በማሰማት፣ በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ላይ እየተደረገ ያለዉን ግፍ አወግዘዋል። ይህ በአንድነት የተጠራዉ ሰላማዊ ሰልፍ ከምርጫ ዘጠና ሰባት በኋላ ሲደረግ የመጀመሪያዉ ሲሆን የአንድነት ፓርቲ ፈር ቀዳጅ የሆኑ ሥራዎችን እየሰራ እንደሆነ እናያለን።

«መንግስት የሕግ የበላይነት ያከብር »፣ «ወ/ት ብርቱካን ያለምንም ቅደመ ሂነታ ይፈቱ»፣ «ወ/ት ብርቱካን ዛሬ ይፈቱ»፣ «ወ/ት ብርቱካንን በማሰር አንድነትን ማዳከም አይቻልም»፣ «ወ/ት ብርቱካን የሕሊና እስረኛ እንጂ ወንጀለኛ አይደሉም» ..የሚሉ በርካታ መፈክሮችን አንግበዉ ነበር ሰልፈኞቹ ድምጻቸዉን ያሰሙት።

በሰልፉ የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ እናት ወ/ሮ አልማዝ ገብረእግዚአብሄር እንዲሁም ኢንጂነር ግዛቸዉ ሽፈራዉ፣ ዶር ያዕቆብ ኃይለማሪያም፣ ዶር ኃያሉ አራያና በርካታ አንጋፋ የአንድነት ፓርቲ አመራር አባላት በሰልፉ ተጀምሮ እሰከሚያልቅ የነበሩ ሲሆን በርካታ ወጣችና ሴቶችን ያቀፈ ሰልፍ ነበር።

ሰልፉ ሊደረግ የነበረዉ ከሁለት ሳምንት በፊት ነበር። ነገር ግን አገዛዙ፣ ሰልፍ ማድረግ እንደማይቻል አሳወቀ። ሰልፍ፣ ፍቃድ ባለመገኘቱ፣ ተላለፈ። ከሳምንት በኋላ ሰልፍ እንደሚደረግ የአንድነት አመራር አባላት ለባለስልጣናቱ አሳወቁ። ሰልፍ ማድረግ እንደማይቻል ባለስልጣናቱ ለአመራር አባላት በቃል ተናገሩ። የአንድነት አመራር አባላት ግን ሰልፍ ማድረግ እንደማይችሉ በጽሁፍ ካልተነገራቸዉ እንደማይቀበሉ አሳወቁ። ባለስልጣናም በጽሁፍ ለመከልከል ፈቃደኛ ስላልሆኑ ሰልፉ ለሁለተኛ ጊዜ በታሰበበት ቀን ተከናወነ። በተሳካም ሁኔታ ተጠናቀቀ።



«ሰልፉ ለምን ሁሉን አቀፍ አልሆነም ? ለምን በሚያዚያ 30 1997 እንደተደረገዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ እንዲገኝ አልተደረገም ? ለምን በመቶዎች ብቻ እንዲገኙ ተደረገ ? » የሚሉ ጥያቄዎች ከአንዳንድ ማእዘናት ይነሳሉ።

ለሶስት ቀን ምግብ ያልበላ ሰዉ ቆሎ ሲቀርብለት «ለምን ክትፎ አልሰጣችሁኝም» ብሎ የቀረበለትን ጥሎ አይሄድም። አምስት ሳንቲም የሌለዉ ሰዉ አምስት ብር ሲሰጠዉ «ለምን መቶ ብር አልተደረገልኝም» ብሎ አምስት ብሩን ጥሎ አይሄድም። ወደፊት ከትፎ ማግኘት የሚቻልበትን መንገድ እየፈለገን ቆሎዉን መቆረጠም፣ ወደፊት መቶ ብር ለማስገባት እየጣርን አምስት ብሯን ወደ ኪስ ማድረጉ ነዉ የሚሻለዉና የሚበጀዉ።

የአንድነት ፓርቲም ያደረገዉ ይሆንኑ ማስተዋልና ጥበብ የተሞላበት ድርጊት ነዉ። ፓርቲዉ ባደረገዉ በዚህ የመጀመሪያና የተቀናበረ ሰላማዊ ሰልፍ ያገኛቸዉ በርካታ ጥቅሞች አሉ። በመቶ የሚቆጠሩ ሰልፈኞች በድፍረት ፣ «ብንታሰርም እንታሰር» ብለዉ፣ ከወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ጎን እንደተሰለፉ ለመግለጽ፣ በአደባባይ መዉጣታቸዉ በመላዉ ኢትዮጵያ የሚኖሩ ወገኖቻችችን ከፍርሃት እንዲላቀቁና በዉስጣቸዉ ድፍረት እንዲኖራቸዉ የሚያደርግ ነዉ አዎንታዊ እርምጃ ነዉ። ከትላንት ወዲያ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ብቻ ነበረች ፊት ለፊት ገዢዉ ፓርቲ የተጋፈጠችዉ። ትላንት በመቶዎች የሚቆጠሩ «ብርቱካን ሚድቅሳዎች» የአዲስ አበባን ከተማ አናወጧት። ባለመኪናዎች የመኪናቸዉን ጨኸት አሰሙ። ነገ ሚሊዮኖች ድፍረት ያገኛሉ። አንድ ተብሎ ነዉ ወደ ሁለት የሚኬደዉ።

ሰላማዊ ሰልፉን የተለያዩ የአለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃን በሰፊዉ የዘገቡት ሲሆን፣ የወ/ት ብርቱካን ጉዳይ በአለም አቀፉ ሕብረተሰ ዘንድ እንደገና ትኩረት እንዲሰጠዉ ለማድረግ ተችሏል።

የሚቀጥለዉ እርምጃ ሕዝብን በማደራጀትና በአንድነት በማንቀሳቀስ፣ ከያሉበት ቦታ ሚሊዮኖችን ፣ በአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን ከወልወል እስከ አሶሳ፣ ከአዲግራት እሰከ ሞያሌ በመጣርት ሰላምዊ ጨዋነት የተሞላበት ሰልፎች እንዲደረጉ ማድረግ ነዉ።

ለዚህም በመላዉ አለም የምንገኝ ኢትዮጵያዉያን ከመናገርና ከማወራት አልፈን ፊት ለፊት አምባገነኖችን እየታገሉ ካሉ፣ በጠበበዉ የፖለቲካ ምህዳር ሕዝባችን ለመብቱና ለነጻነቱ እንዲነሳ፣ ከታሰረበት ፍርሃት እንዲላቀቅ፣ ከተለያዩ አቃጫዎች ጥቃት እየደረሰባቸዉም በትጋት ከሚሰሩ የአንድነት አመራር አባላትን ጎን ልንቆም ያስፈልገናል። ብቻቸዉን ምንም ሊያደርጉ አይችሉም። ድጋፋችን ያስፈልጋቸዋል። ትግሉ የሁላችንም ነዉ።

እነዚህ መሪዎች ሊሳሳቱ ይችላሉ። ነገር ግን በፍቅር ሲሳሳቱ እናርማቸዉ። ሊወድቁ ይችላሉ። ግን እጆቻችንን ዘርግተን እናሣቸዉ። ሊዝሉ ይችላሉ፤ ግን እንደግፋቸዉ። በጋራ በአንድነት ብዙዎች የሞቱለትን፣ ብዙዎች የተሰዉለትን ትግል ከግቡ እናድርስ !

አትላነታ * ቦስተን * ችካጎ * ዳላስ * ዴነቨር * ሎሳንጀለስ* ላስቬገስ * ሚኒያፖልስ * ናሽቪል *
ኦክላነድ * ኦሃዮ * ፊኒክስ * ሳንሆዜ * ሲያትልን * ደቡብ ዳኮታ * አፕ ሰቴኢት ኒኦርክ *
ዋሽንግትን ሜትሮ

ለአንድነት ለዲሞክራሲ ለፍትህ ፓርቲ ( ቅንጅት) በሰሜን አሜሪካ ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች መሀበር
766 Rock Creek Church Rd., NW .Washington DC, 20010 *ስልክ (202) 541-0556
ፋክስ: (202) 541-0557.*ኢሜል: kinijitna@kinijitna.org
Www.kinijitna@kinijitna.org

አስተያየቶን በ awdethiopia@gmail.com ይጻፉልን